# ዲሞክረሲ ‘ወፌ ቆመች…’

**ታሪኩ አባዳማ ግንቦት 2001**

የወያኔው ጠ/ሚኒስትር በዚያን ሰሞን እንዳላገጠው ‘እኛ የፈጠርነው ዲሞክራሲ ለደርግ ባለስልጣናትም ተርፏል’ ብሏል። የተነሳሁበትን ጉዳይ ስለሚያስተኝ ‘እኛ የፈጠርነው…’ የሚለውን ሀረግ ስቄ ባልፍ ይሻላል። እንደርሱ አባባል ወያኔን ሰንጎ እስትንፋስ ያሳጣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ‘ደርግ’ ነው። እነ ሺብሬ ደሳለኝ ሳይቀሩ ፣ እነ ተስፋዬ ማሩ ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ እና ቴዲ አፍሮ ‘ደርግ’ ናቸው። አምቢ ለጎጠኛ ብሎ ለነፃነቱ የተሰለፈ ፣ አንድነትን የሰበከ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ‘ደርግ’ ነው። አሞራን ጅግራ ብሎ መብላት የወያኔ ልዩ ባህሪ ስለሆነ ብዙም አልገረመኝ።

ነገሩን መጀመሪያ ስሰማ ግምቴ እስር ላይ ስላሉት የደርግ ሹማምንት የሚናገር መስሎኝ እነ ሀምሳ አለቃ ለገሰ ምን አዲስ ነገር አግኝተው ይሆን ማለቴ አልቀረም ነበር። አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች በሙሉ ‘ደርግ’ ናቸው ማለቱ እንደሆነ የተረዳሁት ኋላ ነው። ነገር ቶሎ አይገባህም እንዳትሉኝ ፣ ያውም የወያኔ ነገር - ፀሐይ የሞቀው ሸፍጥ።

ያሻውን ገድሎ ፣ ያሻውን አሥሮ - አስበርግጎ እና አሸማቆ ህዝብን መግዛት ከቶውንም ለህጋዊነት ወይንም ለዲሞክረሲያዊ ባህል ማበብ መሠረት ሆኖ አያውቅም። ይልቁንም የህዝብን አንደበት በብረት ሀይል ሸብቦ እኔ ያልኩት ብቻ ‘እውነት ነው’ ማለት የአምባገነኖች ልዩ መታወቂያ ነው። ህዝብ ለወያኔ ሥርዓት ሆነ መሪዎች ፣ ለሚናገሩትም ሆነ ለሚዘባርቁት ዲስኩር ቅንጣት ግምት የማይሰጥ መሆኑ ምስጢር አይደለም። ወያኔ እነደማንኛውም አምባገነን ሀይል ተቀናቃኞችን ስም እያወጣ ለማንኳሰስ ፣ ለማዋከብ እና ለማሸሚጠጥ ቢሞክር ሊገርመን አይገባም ለማለት ነው። ባህሪው ይኸን እንዲፈፅም ያስገድደዋልና።

መሆኑን ደርግ ማለት ‘ተራራ አንቀጥቅጠው’ የጣሉት ሥርዓት አይደለም እንዴ? የጠ/ሚንስትሩን ማላገጥ በጥሞና ካየነው ግን ‘ተራራው ቢንቀጠቀጥም’ ደርግ ባለበት ፀንቶ እየሞገተው ነው። ሰውየው በደመ-ነፍስ (sub-conscious) የተናገረው ካልሆነ በስተቀር የደርግ መንፈስ እንቅልፍ ነስቶታል ያሰኛል። ካስራ ስምንት አመታት ጎጠኛ የጭካኔ እና የከፋፍለህ ግዛ ዘመን በኋላ ‘ደርግ’ን ዛሬም እየታገልነው ነው ሲሉ ግን በወያኔ አይምሮ የንቅስቃሴ ሂደት ሕግ (the law of motion) አይሰራም ማለት ነው። ጉዳዩን ይበልጥ እንዳንረዳ ደግሞ ‘ተራሮቹ ተንቀጠቀጡ እንጂ አልተደረመሱም’ የሚል ፕሮፓጋንዳ የሚፅፍላቸውን ካድሬ አስኮርፈው ስደት ልከውታል። በወያኔ ስሌት እሱም ወደ ‘ደርግ’ ሂሳብ ተጠቃሏል።

ጉዳዩ ፣ አንድም ፌዝ ወይም ፖለቲካዊ ሽሙጥ ቢመስልም መለስ ዜናዊ ስለሚመካበት እና ሞልቶ ለደርጎች ስለተረፈው የወያኔ ዲሞክረሲ ሲናገር ሳያክልበት የቀረ ብዙ ጉዳይ እንዳለ ለማስታወስ እወዳለሁ። ከብዙ በጥቂቱ ለማንሳት ያህል፦ ትናንት በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል የሲያድ ባሬ ወረራ ወቅት ኮለኔል እና ጀነራል ሆነው መንደር ሲያቃጥሉ እና ዜጎችን በጭካኔ ሲያርዱ የነበሩ ባዕዳን ወራሪዎች በወያኔ ዘመን ጥይት ሳይተኩሱ አገራችንን በመቆጣጠር ፣ በኦጋዴን የሶማሊያ ክልል ‘ክቡር’ መሪዎች ተብለው መሾማቸው የአገራችን ታሪካዊ ጠላቶች ሳይቀሩ የወያኔ ዲሞክረሲ ተጠቃሚ ለመሆን እንደበቁ የሚያረጋግጥ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

በወያኔ ዲሞክረሲ ያልተጠቀመ ማን አለ? ኤርትራ “ነፃነቷን” የተጎናፀፈችው በወያኔ ዲሞክረሲ አይደለም እንዴ? ‘የኤርትራን ነፃነት ከኤርትራውያን ይልቅ ያቀላጠፍነው እኛ ነን - እናም እንደ አይናችን ብሌን እንጠብቀዋለን’ ሲል የተሰማው ወያኔ ፤ ‘የኢትዮጵያን ህዝብ በጎጥ ‘ነፃ’ ያወጣነው እኛ ነን። እናም ጎጣዊ ፖለቲካ እንዳይፈርስ እኛ በሥልጣን ለዘላለም መኖር አለብን። አለበለዚያ…’ በሚል ማስፈራሪያ ለዕድሜው መራዘም ባሩድ የሚሰንቅ መንግሥት ስለ ዲሞክረሲ የሥልጣን ባህል ሊሰብከን ባይከጅል ሸጋ ነበር።

ሱዳንስ ከምዕራብ የኢትዮጵያ ድንበር የኔ ያለችውን ክልል ጠቅልላ የወሰደችው በዚሁ ዲሞክረሲ ተጠቅማ መሆኑ አይደለም?። ጠ/ሚኒስትሩ “ከኢትዮጵያ ድንበር ተቆርሶ ለሱዳኖች የተሰጣቸው በአግባቡ ነው” ሲል በአሻንጉሊት ፓርላማው ፊት በቁጣ እና በድፍረት የደሰኮረው ይህን ዲሞክረሲ ምርኩዝ በማድረግ ጭምር ነው። ድንበር ለምን ተደፈረ እያሉ የሚወተውቱ ‘ነፍጠኞች ፣ ትምክህተኞች’ የሚጋለጡትም በተትረፈረፈው የወያኔ ዲሞክረሲ ነው። ለወያኔ ዲሞክረሲ ምስጋና ይግባውና መለስ ዜናዊን የሚያክል ፀረ-ኢትዮጵያ ነፍሰ ገዳይ ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ጭምር መብት ሰጥቷል። የወያኔ ዲሞክረሲ እንኳንስ ሌላ ለጂቡቲ ገገሮችና እና ለሳውዲ ቱጃሮች ሳይቀር ባለውለታ ነው - የሩዝ መዝሪያ ፣ የአበባ ማብቀያ ሰፋፊ ክልል እየገመሰ በመለገስ። ስለወያኔ ዲሞክረሲ ብዙ ማለት ይቻላል።

መለስ ዜናዊ ስለ ወያኔ ተክለ-ፖለቲካ ሲገልፅ ሁልግዜ ጆርጅ ኦርዌል የፃፈውን “1984” ያስታውሰኛል። እንደ ጆርጅ ኦርዌል አገላለፅ በዲሞክረሲ ስም የሚያላግጡ ጨካኝ አምባገነኖች ሥልጣን ከመዳፋቸው እንዳይወጣ ማንኛውንም ሸፍጥ እና ጭካኔያዊ አፈና ከመጠቀም አይመለሱም። ለአምባገነኖች ፣ ሥልጣን በተገኘው ዘዴ ሁሉ ተከብሮ

የሚጠበቅ በራሱ ግብ እንጂ ወደ ግብ የሚያደርስ መሣሪያ አይደለም። ወያኔ ደጋግሞ የነገረን ይህን ያረጋግጣል፡ 'ደም አፍሰን ሥልጣን የያዝነው በድምፅ ለማስረከብ አይደለም' ተብለናል። ዲሞክረሲ ማለት ሥልጣን በሰላም መረካከብ ማለት መሆኑን እዚች ዘንድ ጠቆም ማድረጉ ድንጋይ ላይ ውሀ እንደማፍሰስ ባይቆጠርብን!!

በኦርዌል መፅሀፍ ይበልጥ እንደተብራራው 'የፍቅር ሚኒስቴር' (ministry of love) የተሰኘው መንግስታዊ መሥሪያ ቤት ጭካኔ የተመላበት ምርመራ የሚከናወንበትና በተቃዋሚነት የሚጠረጠሩ ሁሉ ፍዳ የሚቆጥሩበት ቦታ ነው። ለወያኔ - 'ሰላም' (peace) ማለት ከዜጎች ጋር የሚካሄድ የማያባራ ጦርነት ነው ፤ ነፃነት ማለት ባርነት ነው ፣ ጨለምተኝነት እና ማይምነት የጥንካሬ ምንጭ ናቸው። መዝገበ-ቃላቱ አዲስ ወያኔአዊ ትርጉም ተላብሷል። ወያኔ ከሁሉም የአገሪቱ ክልል ህዝብ ጋር እየተዋጋ ነው። ጋምቤላ ፣ ኦጋደን ፣ ወለጋ እና ሐረር ፣ አዲስ አበባ እና ሀዋሳ…ወዘተ። ይህን ለማረጋገጥ ሩቅ መጓዝ አያስፈልግም - ያለአንዳች ፍርድ ፣ 'አሸባሪ' እየተባሉ በሰቆቃ ወህኒዎች ለዓመታት የሚማቅቁትን አሰርት ሽህዎች ማሰቡ ብቻ ይበቃል። ዘመድ አዝማድ የት እንደደረሱ የማያውቃቸው ሽህ በሽህ ናቸው። ወያኔ እንደ መልአከ-ሞት ሌሊት በጨለማ ቀን በቀትር ያሻውን እየጎተተ ይወስዳል። 'ዲሞክረሲው እንዲፋፋ' የንፁሀን ደም ግብር ይገባለታል - እናም በሂደት ላይ ነን ይባላል።

በወያኔ ዘመን መንግስትን መቃወም ብቻ ሳይሆን ስለ ወያኔ አሉታዊ አመለካከት እንዳለው የሚጠረጠር ሁሉ ወንጀለኛ 'ደርግ' ነው። እንደ ኦርዌል አገላለፅ ከሆነ 'thought crime' means that just thinking something bad about the government is as bad as actually committing an offence. ሽብር እና ግርግር በነገሰበት ፣ ሸፍጥ እና ሤራ በተንሰራፋበት ፣ ጎጠኝነት መንግስታዊ ፖሊሲ ሆኖ በሚሠራበት ወያኔአዊ አገዛዝ ዲሞክረሲ ዘበት ነው።

ጎጠኝነት የሚያምነው በችሎታ ሳይሆን በኮታ ፤ በብቃት ሳይሆን በታማኝነት ፤ በእቅድ ሳይሆን በነሲብ ፤ በብልሀት ሳይሆን በደምፍላት ፣ ለመግባባት ሳይሆን ግራ ለማጋባት ፤ ለድርድር ሳይሆን ለግርግር በመጨረሻም ለዕድገት ሳይሆን ለድቀት መሆኑን በወያኔ አገዛዝ በቂ ግዜ ተሰጥቶት ያየነው ነው። ጎጠኝነት የጨለማ ጉዞ በመሆኑ ለሕዝብ የሚበጅ ሀሳብ ማርቀቅ ሳይሆን በወጉ በማያውቁት ጉዳይ መራቀቅ ያበዛል። በህግ እና በሥርዓት ሳይሆን በሤራ እና በማምታታት ዕለት ተለት የሚውተረተር የመንፈስ ደካሞች የበቀል መሣሪያ ነው።

'ዲሞክረሲ በሂደት የሚገነባ ነው' ሲሉ ሰምቶ ወያኔ በበኩሉ ደጋግሞ ይህንኑ ሲያነሳው ሰምተናል። ይሁንና በጎጥ ፖሊቲካ ዲሞክረሲ እየጎለመሰ ሳይሆን እየኮሰሰ ፤ እየተለጠጠ ሳይሆን እየጎበጠ እንደሚሄድ የወያኔን ያገዛዝ ዘመን እና የቅርቡን የፕሬስ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ያወጠውን አዋጅ በማየት ብቻ መመስከር ይቻላል። ጠዋት ማታ ማዕከላዊ እስር ቤት ስለሚመላለሱት ጋዜጠኞች ፣ የሙያ ማህበራት እና ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ሁኔታ ማስተዋሉ በቂ ይመስለኛል። ያለ ፍርድ በየዱሩ እየተገደሉ የተጣሉ ዜጎችን ማሰቡ ፣ የደህንነት ዋስትና በማጣት አገራቸውን ለቀው ስለሚሰደዱ ዜጎች መናገሩ ብቻ በቂ ይመስለኛል። በጋምቤላ እና በኦጋደን ጭምር በሁሉም የአገሪቱ ክልል በገዛ ቄያቸው የተጨፈጨፉ ፣ በር ተዘግቶ በህይወት እንዲቃጠሉ የተደረጉ ዜጎችን ማሰቡ ይበቃል። የወያኔ ሰለባ የሆኑ ዜጎች ወነጀላቸው 'ደርግ ፣ ነፍጠኛ ፣ ትምክህተኛ…ነው።

የዲሞክረሲ ጥያቄ መሠረታዊ የሰብአዊ መብት ጥያቄ ነው። የወያኔ ተፈጥሮ ደግሞ ይህን ጥያቄ ለማስተናገድ አይፈቅድም። ወያኔ ይህን ጥያቄ ለመፍታት - አቅሙም ፣ ችሎታውም ፣ ዝግጁነቱም የለውም። ልብ ብለን አስተውለን ከሆነ በአስራስምንት ዓመታቱ ወያኔአዊ የጎጥ አገዛዝ ዘመን ዲሞክረሲ በራሱ የማይተነፍስ ያልጋ ቁራኛ ሆኖ በ(life support) ከተዘጋበት ሆስፒታል በመማቀቅ ላይ ነው። ዶክተሩ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ናቸው። በሳቸው መልካም ፈቃድ አርቲፍሻል መተንፈሻው ሳይነቀል እንዲቆይ ሆኗል። ከማለሌት እና ህወሓት ኮሌጆች ባገኙት የላቀ ጥበብ እና ልምድ ህመምተኛውን የሰው ደም እየጋቱ 'ዲሞክረሲ ወፌ ቆመች…' ይሉታል።

ህመምህ ነፍጠኛ ነው ፤ ህመምህ ደርግ ነው ፣ ህመምህ ትምክህተኛ ነው ይሉታል። ዲሞክረሲ በ(life support) እንዲቆይ የተፈለገበት አቢይ ምክንያት አንዳንድ አላዋቂዎች ለምዕራብ ወዳጆቻቸው እያሳጡ አገዛዜን ይሸረሽራሉ ብለው ስለሚሰጉ ነው። እንጂ እንደ ዶክተር ጠ/ሚኒስትሩ ዕምነት ከሆነ ዲሞክረሲ ገና ድሮ ታንቆ ጉድጓድ መጣል ነበረበት። ህመምተኛው ዲሞክረሲ ሌላ አስታማሚ ወይም ጠያቂ አይፈቀደለትም። በድን በመሆኑ ዶክተሩ የሚያዙለትን መድሀኒት ብቻ ለመውሰድ ተገዷል። እሳቸው ደግሞ አስራስምንት ዓመት ሙሉ የሚያዙለት የሰው ደም ብቻ ነው ። ታምር ተፈጥሮ አንድ ቀን ካሸለበበት ቢነቃ በርሶ እጅ ከምታመም ወይ እርሶ ወይ እኔ ብንገላገል ይሻላል ማለቱ አይቀርም። በምርጫ 97 ትንሽ አገግሞ ካንገቱ ቀና ሲል የሆነው ይኸው ነበር።ዲሞክረሲ life support ቱን ነቃቅሎ ፣ የሆስፒታሉን በር በርግዶና ሀኪሙን አሽቀንጥሮ በነፃ እና በራሱ ለመተንፈስ ያለውን ፅኑ ምኞት ያሳየበት አጋጣሚ። በዶክተሩ ጥብቅ ትዕዛዝ ይህ ሀያል መንፈስ ዳግም እንዳያንሰራራ አልጋ ላይ ተኝቷል። ሀያሉ ዲሞክረሲ ዛሬም በወያኔ እጅ በድን ሆኗል።